ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

---

*አስቸኳይ መግለጫ*

# በኢትዮጵያ የመሬት ነጠቃና ነዋሪውን በግዳጅ የማፈናቀል ተግባር

*ከመንግሥት እጅ ያፈተለከ መረጃ*

*‹‹የጋምቤላ ሕዝቦች ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የመንደር ምሥረታ መርሃግብር (2003ዓ.ም.)››*

በቅርቡ ህወሃት/ኢህአዴግ ከሚመራው አገዛዝ እጅ ያፈተለከ መረጃ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ እጅ ገብቷል፡፡ በንቅናቄያችን እጅ የሚገኘው ይህ መረጃ ርዕሱ *‹‹የጋምቤላ ሕዝቦች ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የመንደር ምሥረታ መርሃግብር (2003ዓ.ም.)››*[1] የሚል ሲሆን በመጪው ዓመት ከጋምቤላ ክልል 49 ‹‹መንደሮችን የማስፈር ተግባር›› ላይ ያነጣጠረ መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ ከእነዚህ መንደሮች የሚፈናቀለው ሕዝብ በአማካይ 225,000 የሚሆን ሲሆን ይህም በድምሩ 45,000 የቤተሰብ መሪዎችን የሚጠቀልል ነው፡፡

ይህ ነዋሪዎችን የማፈናቀል ተግባር በጋምቤላ ክልል ላይ ያነጣጠረ ብቻ ሳይሆን በአፋር፣ በኦጋዴን እና በቤንሻንጉል-ጉምዝ ክልሎችም በተመሳሳይ መልኩ የታቀደ መሆኑን የታመኑ የዜና አውታሮች እንዲሁም ‹‹ብሉምበርግ›› የተሰኘው ድረገጽ ከዚህ በፊት ዘግበዋል[2]፡፡ በዚህም መሠረት ከእነዚህ ክልሎች በአጠቃላይ ከ150,00 የቤተሰብ መሪዎችን (ከ750,000 በላይ ነዋሪዎች) ያካተተ የሰፈራ ፕሮግራም የታቀደ መሆኑን የዜና ምንጩ ጠቅሷል፡፡ በአቶ መለስ የሚመራው ጠባብ ብሔረተኛ አገዛዝ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ በመቶ ሺዎችና ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን በግዳጅ መሬታቸውን እየነጠቀ እትብታቸው ከተቀበረበትና ለአያሌ ዘመናት ተከብረው ተዋልደው ከኖሩበት ቀዬ እያፈናቀለ መሬቱን ለውጪ ባለሃብቶች እየሰጠ ይገኛል፡፡

---

[1] http://www.anuakjustice.org/downloads/VillagizationProgramActionPlan(2003).pdf
2 http://addisvoice.com/2010/11/ethiopian-govt-relocates-somalis-bloomberg/



ስዕል1. ከሚፈናቀሉት በርካታ መንደሮች መካከል አንዱ

ከጋምቤላ የሚፈናቀሉት ከተለያየ ቀበሌ ተሰባስበው በአብዛኛው ወደ አንድ ቦታ እንዲሰፍሩ የታቀደ ሲሆን በተለይም ለእርሻነት እየተሸጡ ወዳሉት ሰፋፊ መሬቶች አካባቢ ጣጋ እንዲሉ ያስፈለገበት ምክንያት በርካሽ የጉልበት ሠራተኛነት እንዲያገለግሉ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡ በድርጊት መርሃግብሩ ላይ ለ45,000 የቤተሰብ መሪዎች በነፍስወከፍ ከ 3 እስከ 4 ሄክታር ይሰጣል የሚል መረጃ የሰፈረ ቢሆንም እነዚህ የቤተሰብ መሪዎች እንዲሰፍሩበት የተመደበው 60,000 ሄክታር መሬት በመሆኑ መርሃግብሩ ላይ እንደተባለው ሰፋሪዎቹ የሚያገኙት ከ3 እስከ 4 ሄክታር መሬት ሳይሆን ከ1.3 ሄክታር በታች የሆነ መሬት ብቻ እንደሆነ ነው፡፡



ስዕል2. የሶስት መንደር ነዋሪዎች ለዚህ ዓመት የተከሉት የማሽላ ሰብል በጥቂቱ ይህንን ሲመስል በመርሃግብሩ መሠረት ከቀያቸው ሲፈናቀሉ እንዲህ ያለውን ምርታቸውን ጭምር ትተው ነው የሚሄዱት፡፡

ይህ በህወሃት/ኢህአዴግ የተዘጋጀው መርሃግብር በጥንቃቄ ላነበበው በራሱ የተለያዩ ችግሮች ያሉበት ነው፡፡ በአንዳንድ ገጾች ላይ የሰፈራ ፕሮግራሙ በዕቅድ ተይዞ የሚከናወን መሆኑን ይገልጽና በሌላ ቦታዎች ደግሞ ሰፋሪዎቹ ወደዱም ጠሉ ወደሰፈራ መንደሮቹ እንደሚነሱ ያትታል፡፡ በሌላ ቦታ ደግሞ ለነዋሪዎቹ አስፈላጊ የሆኑት የመሠረተ ልማት አውታሮች ከሰፈራው በፊት እንደሚዘጋጅላቸው ይጠቅስና በሌላ ቦታ ላይ ደግሞ ዕቅዶችን ተግባራዊ ለማድረግ የገንዘብ እጥረት እንደሚኖር ይጠቁማል፡፡ ምንም እንኳን የመርሃግብሩ ሰነድ ሰፋሪዎች ‹‹በፍቃዳቸው›› እንደሚሰነሱ ቢናገርም ሰፈራውን በመቃወም ድምጻቸውን ያሰሙ የክልሉ ሰዎች ግን ከፍተኛ የሆነ እንግልት፣ ግፍ፣ እስርና ሞት እየደረሰባቸው ይገኛል፡፡



ስዕል3. ካሩቱሪ ዓለምአቀፍ ለተሰኘው የህንድ ድርጅት ሰፊ የእርሻ መሬት ይሆን ዘንድ ለምንጣሮና ሰፈራ ከተዘጋጁት መንደሮች አንዱ፡፡

ህዳር 23፣2003 ዓም በተላለፈው የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የአማርኛው ክፍል[3] ፕሮግራም የኢትዮጵያው የግብርና ሚኒስትር፣ የንቅናቄያችን ዋና ዳይሬክተርና ከጋምቤላ ደግሞ የአኙዋክ ተወላጅ የሆኑት አቶ ማንጎ (ስማቸውን ቀይረው) የተባሉ ግለሰብ ቃለመጠይቅ ባደረጉበት ወቅት የግብርና ሚኒስትሩ ያልተገኙ ቢሆንም አቶ ማንጎ ግን በቦታው ላይ ያለውንና የሰፈራውን ሁኔታ ግልጽ በሆነ መልኩ አስረድተው ነበር፡፡ በመቀጠልም አቶ ማንጎ የተናገሩት *‹‹በአገራችን እየተካሄደ ስላለው ሁኔታ ለመናገር እንድችል ለሰጣችሁኝ ዕድል አመሰግናለሁ፤ እኔ አሁን ደስተኛ ነኝ፡፡ ከእንግዲህ በኋላ ብሞት እንኳን ምንም አላዝንም ለዓለም እውነቱን ከተናገርኩ በኋላ ስለሚሆን እንዲያውም ደስተኛ ነኝ››* የሚል ነበር፡፡

አቶ ማንጎ ይህንን ቃለመጠይቅ ከሰጡ በኋላ በአገዛዙ በኩል በድምጻቸው ብቻ ማንነታቸውን ለማወቅና ለማሰር ጥብቅ ክትትል ሲደረግ ቆይቶ ነበር፡፡ በቅርቡ በደረሰን መረጃ መሠረት የአቶ ማንጎን ማንነት የአገዛዙ ሰላዮች በማወቃቸው

[3] http://www.voanews.com/amharic/audio/

ታህሳስ 25፣2003 ዓም አቶ ማንነ በቁጥጥር ሥር ከዋሉ በኋላ በአሁኑ ወቅት የደረሱበት ቦታ እንደማይታወቅ ለመረዳት ችለናል፡፡ በእርግጥ ያፈተለከው መረጃ መርሃግብር እንደሚለው የሰፈራው ፕሮግራም ሕዝቡን ለመጥቀም ታስቦ የተደረገ ከሆነ ለምንድነው ድምጻቸውን የሚያነሱ የአካባቢው ነዋሪዎች ላይ እንደዚህ ዓይነት ጥቃት የሚደርሰው ብለን እንድንጠይቅ እንገደዳለን፡፡ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ እንደዚህ ዓይነት ተግባር መፈጸም ዓይነተኛ መለያ ባህሪው እንደሆነ በተደጋጋሚ የተረጋገጠ ነው፡፡ ለይስሙላ ዴሞክራሲ በማለት ቢለፍፍም በተግባር ግን የሚያደርገው ሰብዓዊ መብትን መርገጥ፣ ምርጫን ማጭበርበር፣ ጋዜጠኞችን ማፈንና ማሰር፣ የዘመኑ ቴክኖሎጂ ያፈራቸውን የመገናኛ መንገዶችን መሸበብ፣ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን ማስፈራራት፣ ማሰር፣ ማፈን፣ ኢትዮጵያውያንን ከተወለዱበት መሬት ማፈናቀል፣ መሬታቸውን መንጠቅ፣ እንደ ኦጋዴን እና ጋምቤላ ባሉ ክልሎች ደግሞ የዘር ማጥፋትን ጨካኝ ወንጀሎችን መፈጸም ነው፡፡



ስዕል4. አገዛዙ እንደሚለው ሳይሆን ከመኖሪያቸው የሚፈናቀሉት ቤተሰቦች ኑሯቸውን ከምንም መጀመርም ይሁን የመኖሪያ ጎጇቸውን መሥራት የራሳቸው ኃላፊነት ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ በጋምቤላም ሆነ በሌሎች ክልሎች የሚደረገውን የአሰገድዶ ማስፈር ተግባር የሚቃወሙ በአገዛዙ አፈና እና እንግልት እየደረሰባቸው ቢሆንም ይህ አፈና ጊዜውን ጠብቆ መጠነሰፊ በሆነ ሁኔታ መፈንዳቱ እንደማይቀር የጥቂቶች ብቻ ግምት አይደለም፡፡ ኢትዮጵያን ጎብኝተው የሚመለሱ የውጪ ዜጎችም ይህንኑ እውነታ እያረጋገጡ ቢሆንም አገዛዙ ግን ከሳውዲ አረቢያና ከህንድ ባለሃብቶች ለጊዜያዊ ችግሩ መጠቀሚያ የሚሰበስበው የውጪ ምንዛሪ ብቻ ስለሆነ የሚታየው እውነታውን እየካደ ይገኛል፡፡

በቅርቡ አዲስ ተመራጩ የውጭጉዳይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ ከህንድ ቴሌቪዥን ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ[4] ከመሬት ነጠቃው ጋር በተያያዘ ወደፊት ከህዝብ ሊመጣ ስለሚችል ተቃውሞ ምን ዋስትና ሊሰጡ እንደሚችል ሲጠየቁ

[4] http://www.youtube.com/watch?v=_IjnseXIt2w&feature=player_embedded

የመለሱትን ማዳመጡ ብቻ ይህ አገዛዝ አስተዳድረዋለሁ ለሚለው ሕዝብ ምንያህል ደንታ እንደሌለው የሚያመላክት ነው፡፡ አቶ ኃይለማሪያም ስለሕግ የበላይነት፣ ስለ ዴሞክራሲ በቃለመጠይቁ የተናገሩት የህወሃት/ኢህአዴግ ማንነትን ለሚያውቅ ሰው በሚቃጠል ሜዳ ላይ የሳር ጎጆቤት ሠርቶ እኖራለሁ ብሎ እንደሚያስብ ሞኝ ነው የሚቆጠረው፡፡



ስዕል5. ወዴት እንደሚሄዱ የማያውቁ መንደረተኞች የመኖሪያ አካባቢያቸው በሙሉ ለሳውዲ ኩባንያ በመሰጠቱ እስካሁን እየጠበቁ ይገኛሉ፡፡

መሬታቸው ሊነጠቅባቸው ከታቀዱት አንዱ በሆነው በቤንሻንጉል-ጉምዝ የሚኖር አንድ አባወራ የተናገረውን እዚህ ላይ መጥቀሱ የሁኔታው አሳሳቢነት በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ *‹‹ሰላም ሊመጣ የሚችልበት መንገዶች ሁለት ብቻ ናቸው፡፡ አንዱ ሁላችንንም ከአፈሩ በታች ቀብረውን እነሱ የፈለጉትን ሲያደርጉ፣ ማለትም እኛ ከአፈር በላይ ሆነን መሬታችን በኃይል ተነጥቆ ሊወሰድ አይችልም፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የአካባቢው ነዋሪ በጉዳዩ ላይ እንዲመክር ዕድል ተሰጥቶትና በጉዳዩ ላይ ተሳታፊ እንዲሆን ተደርጎ ለነዋሪውም ሆነ ለባለሃብቶቹ በሚጠቅም መልኩ የውሳኔ ሃሳብ ላይ እንዲደረስ ሲደረግ ብቻ ነው፡፡ ማንም ቢሆን ሰው ቤት ገብቶ ኑሮዋችሁን በዚህ መልኩ ነው መኖር ያለባችሁ ብሎ ትዕዛዝ ቢሰጥ የቤቱ ባለቤቶች ዝም ቢሉ ተስማምተው ሳይሆን ተገድደው መሆኑን ማንም የሚክደው ሐቅ አይደለም፡፡››*



ስዕል6. ከመኖሪያቸው እንዲነሱ የተነገራቸው አባወራዎች አዲስ ወደሚሄዱበት ቦታ የራሳቸውን መኖሪያለመሥራት እንዲዘጋጁ መመሪያ ሲሰጣቸው፡፡

በኢትዮጵያ የተለያዩ ክልሎች እየተካሄደ ያለው የመሬት ነጠቃ የፈጠራ ነገር ወይም ለዜና ፍጆታ ሆን ተብሎ የሚደረግ ሳይሆን በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ እየተፈጸመ ያለ እውነተኛ ድርጊት ነው፡፡ የአፍሪካ አህጉርን መዝረፍ ለዘመናት ሲካሄድ የኖረ ተግባር ነው፡፡ በዚህ ዝርፊያ ዋነኛ ተዋናዮቹ ደግሞ የአህጉሩ መሪዎች ናቸው፡፡ ራሳቸው በህገወጥ መንገድ ሥልጣን ይዘው የአገርን ሃብት ለሃምሳና መቶ ዓመት በርካሽ ሲወረውሩ ቅንጣት ታህል አያስቡም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ተግባር የሚፈጸመው እንደኢትዮጵያ ባሉ የአፍሪካ አገሮች ብቻ ነው እንጂ በምዕራቡ ዓለማትማ ፈጽሞ የማይታሰብ ነው፡፡ አሁን ጊዜያዊ ጥቅማቸውን የሚመለከቱት ድርጅቶች ደግሞ ራሳቸውን ከአምባገነን አገዛዞች ጋር በማበር የወንጀል ተግባር ሲፈጽሙ ነገ በሕዝብ የተመረጠ ነጻ መንግሥት የተመረጠ ጊዜ ይህ ሁሉ ውል ተቀባይነት እንደሚያጣ ጥቂት ሊያስቡት አለመቻላቸው በጊዜያዊ ጥቅም ምንያህል የታወሩ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡




ስዕል7፣8. የአላሙዲ ሳዉዲ ስታር ኩባንያ ለምንጣሮ፣ እርሻ፣ ወዘተ ሊጠቀምባቸው በ10,000 ሄክታር ላይ የደረደራቸው ትራክተሮች፣ ቡልዶዘሮች እና ሌሎች ከባድ መኪናዎች ስብስብ፡፡

መሬታቸው ተነጥቆ ለሰፋፊ እርሻዎች ባለሃብቶች ሊሰጥ ባሉባቸው ክልሎች አንዱ በሆነው የጋምቤላ ክልል ነዋሪ የሆነ አንድ አኙዋክ አባወራ የተናገረውን አገዛዙም ሆነ ባላሃብቶቹ ልብ ሊሉት ይገባል፡፡ ‹‹*እነዚህ ባለሃብቶች እኛን ከአያትና ቅድመ አያቶቻችን መሬት በግዳጅ አስነስተው የራሳቸውን ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን በማረስ አምርተው ይሳካልናል ብለው የሚያስቡ ከሆነ ፍጹም ተሳስተዋል፡፡ ሊሳካላቸው*

*የሚችልበት ብቸኛው መንገድ ሰብላቸው አረንጓዴ ሆኖ መቆየት ሲችል ብቻ ነው፡፡››*



ስዕል9. በእርሻዎች መካከል ለምንጣሮና ለመጓጓዣ እንዲሆን አዲስ እየተሰሩ ያሉ ጥርጊያ መንገዶች፡፡

ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ የውጪ ባለሃብቶች ቆም ብለው ሊያስቡና ከእንደዚህ ዓይነት አፓርታይድ መሳይ አገዛዝ ጋር ያላቸውን ወይም ሊጀምሩ የሚያስቡትን ግንኙነት ደግመው ሊያስቡበት ይገባል፡፡ በሚያደርጉት ማናቸውም ዓይነት ውል የህዝቡን ይሁንታ የሚያገኙበትን መንገድ መፈለግና የነዋሪዎችን ጥቅም ሊያስከብር የሚችል ተግባራት ላይ ቅድሚያ ሊሰጡ ይገባል፡፡ ከጊዜያዊ ጥቅም በላቀ መልኩ ዕውነትን፣ ፍትህን እና ነጻነት በመደገፍ ከእነዚህ ታላላቅ መርሆዎች ጋር ሊቆሙ ይገባቸዋል፡፡ መንግሥታትና ጨቋኝ አገዛዞች በጊዜያቸው ይከስማሉ ሕዝብ ግን ለዘላለም ይኖራል፡፡ ከሕዝብ ጋር መተባበርና ለሕዝብ መቆም ዘላቂነት ያለው ብቻ ሳይሆን አማራጭም የሌለው መፍትሔ ነው፡፡

***‹‹መልካም የሆነውን ነገር ብታደርጉና ቅን የሆነውን ነገር ብትናገሩ ትድናላችሁ፡፡ ስለዚህ በሥልጣናችሁ ተመክታችሁ ድሆችን በመጨቆን አትበዝብዙ፡፡ ጉቦ ለመቀበል እጃችሁን አትዘርጉ፤ ሰው ለመግደልም ሆነ ሌላ ክፉ ነገር ለማድረግ ዕቅድ ከሚያወጡ አድመኞች ጋር አትተባሩ፡፡›› ኢሣ. 33፡15***

ይህንን የምናስተውልበት አእምሮ ፈጣሪ ለሁላችንም ይስጠን፡፡ አገራችንንም ከመከፋፈልና ከአደጋ ይጠብቃት፡፡ እኛንም መልካምና እውነተኛ ለሆነው ነገር ሁሉ በሐቅ እንድንቆም መንፈሳችንን ያነሳሳው፡፡

**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ**

*****************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

